# ትግላችን

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
ወርሃዊ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

## የጊኔ ቢሳው ሕዝብ ትግል


የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN



ቁጥር **3**
የካቲት—ሚያዝያ 1963

ዋጋው፡ 1.50 ብር

# ለንባቢዎቻችን

<u>ትግሏችን</u> ዘግይቶ በዚህ ወር በመውጣቱ አዘጋጅ ቦርድ አንባቢዎችን ይቅርታ ይጠይቃል:: ካንዳንድ ቴክኒካዊ ችግሮች የተነሣ

ሀ/ መጽሄቱ ቶሎ ሊደርስ አልቻለም

ለ/ በመጽሄቱ ውስጥ ግድፈቶች አሉ

ሐ/ ከብዙዎች አንባቢዎች የቀረቡልንን ጽሁፎች በሙሉ ለማውጣት ስላልቻልን የግድ አስቸጋሪ የጽሁፍ ምርጫ ማድረግ ነበረብን::

ለዚህ ሁሉ ለጊዜው ካቅማችን በላይ ሆኖ ለተገኘ እንቅፋት: ወደፊት መፍትሄ እንደምናገኝ እያመንን: ሳለፈው አንባቢዎቻችን ይቅርታ እንዲያደርጉልን እንደገና እንጠይቃለን::

ትግላችን

## ያ ገ ር ቤ ት ዜ ና

እኤአ ሰኔ 27/71 በወጣው 'አብዘርቨር' የእን ግሊዝ ጋዜጣ፡ከሊን ሊጋም በጻፈው አምድ መሠረት ከሁለት እስከ አራትሺ የሚገመቱ ያዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች መታሰ ራቸው ታውቋል::በአራት ልዩልዩ ቦታዎች ታጉረው በከባድ መንገ ላታትና ጭካኔ የተያዙ መሆናቸውንም ጨምሮ ይገልጻል::

ከሚታመን ምንጭ ከኢትዮጵያ በተጨማሪ የደረሰን ዜና የሊጋምን ጽሁፍ በሙሉ ከማረጋገጡ በላይ አንዳንድ ተጨማሪ መረ ጃዎችን ሰጥቶናል::

ተማሪዎቹ እርምጃ እንዲወስዱ ያስገደዳቸዉ በህዝቡ ላይ የደረሰው ብዝበዛና ጭቆና ነው::ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ 1/ የከተማው አውቶቡሶች ዋጋ መቀጠል፡ 2/ የቀቤ ዋጋ መቶ በመቶ መጨመር፡ 3/ በጠቅላላውም የኑሮ ዋጋ በአንድ አመት ውስጥ ከሁለት መቶ እስከ አራት መቶ በመቶ ማደግ ናቸው::

ተማሪዎቹ በሰባ ስድስት የሚገመቱ አውቶቡሶችንና የበዝባዡ ወገን የግል መሸከርከሪያዎችን በሚያስገርም ቀልጥ ፍና ወግረው አበላሸተዋል::የወሰዱት እርምጃ በህዝቡ መሠቃ የት በመቀር ቀር ስለሆነ የከተማው ህዝብና ፖሊስም ጭምር በሙ ሉ ደግፈዋቸዋል::አውቶቡሶቹን በወገሩበት ጊዜ የተጠቁበት ያጠቃቀ ስልት የድርጅታቸውን መብሰል በግልጽ ያሳያል::በት ንንሽ ጓደኛ እየተደራጁ በከተማው በልዩልዩ ቦታዎች ተሰማሩ:: ቀደመው የተቃጠሩበትን ጊዜ በትክክል በማክበር አውቶቡሶቹ ቆመው በሚገኙበት ቦታ ሁሉ አደጋ ጣሉ::የአደጋ አጣጣሉ አኗ

ጣጠንና በተለይም የአጥቂው ቡድን አነስተኛነት የጸጥታ ሰራ
ዊቱን ገራ ስላገባው አርምጃ አንዳይወስዱባቸው አስገድዶታል::
አደጋውን በሚጥሉበት ጊዜና ቦታ ሁሉ 'መሬት ላራሹ' እንዲ
ሁም ይሁን የመሳሰሉ መመሪያዎች የሰፈሩባቸው ሰሌዳዎችን ለህ
ዝብ አሳይተዋል::ዋጋ እየቀጠሉ ህዝቡን የሚበዘብዙትን ነጋዴ
ዎች የሚገባቸውን ቅጣት በመስጠት የቀቤ ዋጋ እንዲቀነስ
እድርገዋል::

የንጉሰ ነገሥቱ መንግስት አጅግ ተሸብሮ ነበር::
ይልቁንም ተማሪዎቹ ያደረጉት የጀብዱ ሥራ ሕዝባቸውን
የኢምፔሪያሊስቶች ባሪያ ከሆነው ከንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት
ጭቆናና ከታላቅ ከበርቴዎች ብዝበዛ ነፃ ለማውጣት መሆኑን
የገባው የፖሊስ ሠራዊት ገለልተኛነትን ስለመረጠ መንግሥቱ
በተለይ ደነገጠ:: ጸጥታ ለማስከበር በአዳማ ከተማ የሰፈ
ረውን የምድር ጦርና ታንኮችም አንቀሳቅሶ ከተማውን አስከበበ:
ከሚታመን ምንጭ እንደሰማነው ይህ በሆነበት ጊዜ በመንግሥቱና
በጦር ሠራዊቱ መካከል ትልቅ አለመግባባት ተፈጥሮ ነበር
ይባላል::

የጦር ሠራዊቱ የከተማውን ጸጥታ ጠብቅ ከተባሉ
ሙሉ ሥልጣን ይሰጠኝ ሲል ጠየቀ::/በሌላ አነጋገር:በከተማው
ላይ የወታደር አስተዳደር ይታወጅ ማለቱ ነው::/ ሠራዊቱ
የጠየቀውን ለመቀበል ስለፈራ መንግሥቱ ከየጠቅላይ ግዛቱ
የተውጣጡ የፈጥኖ ደራሽ ቡድኖች አስመጥቶ ተማሪዎቹን በጭካኔ
ለማስጨፍጨፍ ተዘጋጀ:: ነገር ግን ተማሪዎቹ ያቀዱትን ሁሉ
በፍጥነት ግብ አድርሰው ድል ስለነሡ በተማሪዎቹ ላይ ብዙ
አደጋ ሳይደርስ የሽብሩ ጊዜ አለፈ::



በደረሰን ዜና መሰረት ያዲስ አበባ ከተማ በሁለት
መንግሥት ነው የሚተዳደር ቢባል ስህተት አይሆንም ይባላል::
አንደኛው መንግሥት የተማሪዎቹ ሥልጣን ነው::ተማሪዎች በህ
ዝቡ ዘንድ ያገኙትን አቀባበል ለማኮሸፍ በመሞከር መንግሥቱም
ዋጋ ለማስቀነስ ሞክሮአል: ነገር ግን 'ወደሽን ነው' እን
ደሚባለው ሁሉ ይህ ሙከራ ህዝቡን ሊያስደስተው አልቻለም::
ይልቁንም ህዝቡ መንግሥቱን ከመቼውም የበለጠ ጠልቶታል::የተማ
ሪዎቹ ድል መንግሥቱን ከመቼውም የበለጠ በህዝቡና በዓለም ፊት
አጋልጦታል::

የተማሪዎቹ እንደገና መነሣት የኢትዮጵያ ህዝብ ከፊ
ውዳል አገዛዝና ከኢምፔሪያሊዝም ነጻ ለመውጣት የሚያደርገው
ትግል እየተፋፋመ መሄዱን ያሳያል::ህዝቡ ነጻ ወጥቶ ህዝባዊና
ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ካልተመሰረተ ትግሉ አያቋርጥም::

ወንድሞቻችን ጠላታችንን በሚያስደስት አኳኋን ድል
በመንሣታቸው ልባዊ ምሥራቻችንን እንገልጸላቸዋለን::ከኢትዮጵያ
ውጭ ተሠማርተው በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ስም ሆኖ ዓለ
ም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር በትግሉ ከተካፈሉት ተማ
ሪዎችና ከደጋፊዎቻቸው ሁሉ ጋር ያለውን አንድነት ይገልጻል::

የንጉሠ ነገሥቱ አድሀሪ አገዛዝ ተማሪዎቹን በብዙ
ሺህ እየያዘ በማሠር አድሜውን የሚያስረዝም ይመስለዋል::ነገር
ግን ይህ ከንቱ ሙከራ ነው::በብዙ ሺህ የሚቆጠሩትን ከሃያ
ዓመት አድሜ በታች የሆኑትን ወጣቶች ይህ ፋሺስታዊ መንግሥት
በረሃብና በበትር እያሰቃየ ከከተማው ውጭ አስፍሮአቸዋል::
ይህ ጭካኔ የተማሪዎቹን መንፈስ ያደክመዋል ብሎ መንግሥቱ

ከገመተ ተባሰቶአል::እንዲያውም ያጠነከረዋል እንጂ:: የታሠረትን ወንድሞቻችንን እንዲፈታና ወደትምህርታቸው በቶሎ እንዲመለሱ እንዲያደርጋቸው እናስጠነቅቃለን::ባሳባታዊ አገዛዝና ኢምፔሪያሊዝም ከኢትዮጵያ ገጽ የሚጠፋበት ቀን ተቃርቦአል::ማገናቸውም ጭቆናና ወንጀል ከኢትዮጵያ ህዝቦች የቆጧ ማእበል አያድናቸውም::



## ለዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

ትግላችን ቁጥር 2ኛ ዳር-ጥር 1963 ደርሶናል:: መጽሔታችን ከቀድሞ እትሞቹ በተሻለ መንገድ መቅረቡ የሚያስደስት ነው::ይህም ከሰማይ ዱብ ያለ መና አለመሆኑን መረዳት ሲኖርብን ዋናው ምክንያትም በኢትዮጵያ የግፉን የበደሉን በብዛትና መስፋፋት ውጤት ነው:: የሕዝቡ ትግል በያለበት እንደሰደድ እሳት እየሰፋ በሚሄድበት ወቅት: መጽሔቱም የሕዝቡ አፈቀላጤ ሊሁን እስካለ ድረስ: የዓይነት ለውጥ ማድረግ ተገቢው ግዴታ መሆኑን የተፈጥሮ ሕግ ያሳየናል::መጽሔታችን ከዚህ ደረጃ ደርሶ ይሆን?

ይህን መግለጫ ለመስጠት የተገደድንበት ምክያት: በዚሁ መጽሔት ውስጥ የኤርትራ ጥያቄ ስለተወሳና ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ከሚቴውም የኤርትራ ሕዝብ ትግልን በሚገባው መንገድ በተቻለ መጠን የትግሉን ፍቻውን አሳጥቶ በተቻለ መጠን ለማወናበድ በለሞከረ:ይህንንም አይተን ዝም ማለቱ በሕዝብ ትግል ማሾፍ በለመሰለን: ንጹህ መልካቸሁ ከነእቋማቸሁ ለንጹህ የሕዝብ ወገኖች ለማሳየት እንሞክራለን::ይህን ሁኔታ በበለጠ ለማስረዳት ተገቢ ነበር:ግን ለጊዜው በጽሑፍ ብቻ መወሰን ይኖርብናል::

ወደአርእስቱ መለስ ስንል በገጽ 44 እንዲህ ይላል "አድጣሪው መንግሥት የኤርትራን ሕዝብ ትግል በሃይማኖትና በነገድ ልዩነት ላይ የተመሠረተ አድርጎ በማቅረብ ሕዝቡን ለማወናበድ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ

ይታወሳል::ያገነቱ ጥረቱ ሁሉ ከንቱ ሆኖ ቀረ:: የተጨቆነው ሕዝብ እንደዚሁ ባለው መሠረተቢስ ፕሮፓጋንዳ ለረዥም ጊዜ ሊታለል አይችልም::ጭቆናው ገፋ የሚወርድበት የሃይማኖት ወይም የነገድ ልዩነት በመኖሩ ሳይሆን:ዘራፊዎቹ በሥልጣን ላይ በመወዘፋቸው መሆኑን እለታዊ ኑሮውና ትግሉ ያስተምረናል::

በርግጥ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚወበዳቸውን አድኀራዊ አርምጃዎች መቃወሙ ተገቢ ተግባር ነው::ግና "የኤርትራን ሕዝብ ተግል በሃይማኖትና በነገድ ላይ የተመሠረተ አስመስሉ" ትሳሳቸሁ::ጉዳዩ እንደዚህ ነው:: የጭቆና መልኩ በዘና ዝንጉርጉር መሆኑን ተረዱ ይሆን?የኢኮኖሚ ጭቆና መሠረታዊ ጭቆና መሆኑ አይሳትም::በኤርትራ አንድ ቁልጭ ያለ እውነት አለ::የኤርትራ ሕዝቦች ማለትም አብዛኛው:ከኢኮኖሚ ጭቆናው የተለየ የሃይማኖት የቋንቋ ወዘተ. ጭቆና ይደረግበታል::ይህም ሁኔታ ከገዥው ሕዝብ በስተቀር በሌሎች ላይ ይፈጸማል::በኤርትራ ይህ ድርብ ድርበርብ ጭቆና የጠመንጃ ትግልን ወለደለ:: የመንግሥቱ "በሃይማኖትና በነገድ በሚለበት" ወቀት:የናንተም ፉርሽ ፕሮፓጋንዳ ከዚያ ያልተሻለ መርዘና ፕሮፓጋንዳ "መሠረተቢስ ፕሮፓጋንዳ"ይሳል::ጉዱ እኮ ነው::አብዛኛውን የኤርትራን ሕዝቦች ማለት በዝባዡንና ተበዝባዡን ሊያዛምደው የቻለው የኢኮኖሚው ጭቆና ብቻ ነው ልትሉ ነውን?ከመቼ ደምሮ ነው የበዝባዡና የተበዝባዡ ኢኮኖሚ በአንድ ዓይን መታየት የተጀመረው::በርግጥ በጨራዊ ቡርዡዋ የፊውዳል ተጸንአንና የውጭ ባለካፒታልን መቃወሙ ወይም የመቃወም ስሜት እንዳለው እሙን ነው::ይዘታውን ግልጥልጥ አድርገን ስናየው: በኤርትራ ከበርቴውንና ደሀውን ያጣመረው ሊያጣምረውም የሚችለው ከኢኮኖሚ ጭቆና ጋር የባሕል ወዘተ. ጭቆና ሲደ



ባለቀ ነው::አድሐሪው መንግሥት ትግሉን የሃይማኖትና የነገድ ነው በሚለበት ጊዜ የኛ መልሳችን ይህ መሠረተቢስ ፕሮፓጋንዳ ነው ማለት አይደለም:ቁልጭ ያለ እውነት አለ::ይኸውም የኤርትራ ሕዝቦች ሃይማኖታቸን ባሕላቸን ይከበር ማለታቸው ነው::ለሃይማኖታቸን ለባሕላቸን እንዋጋለን ማለታቸውና ደምም መዋጋታቸው ነው:: የኛ መልሳችን መሆን የሚገባው መሠረተቢስ ከማለት ይልቅ መሠረት ያለው ነውና: የማንኛውም ሕዝብ ሃይማኖትና ባሕል ተልቅነት ይከበር ነው:: በኤርትራም እኳያ የኤርትራ ባሕል ሃይማኖት ይከበር ማለት ይኖርብናል:: የኤርትራ ሕዝቦች ሃይማኖት ተነካ ባሕሌ በሌላ ተቀየረ ማለትን እምነን:ይህን ዓይነቱን ጭቆና ማውገዝ ይኖርብናል:: የባሕልና የሃይማኖት ጭቆናን መቃወም አድሐሪ አርምጃ ነው ሊባል ነውን?ጥያቄው ተራማጅ ጥያቄ ነው::ጭቆናን ይቃወማልና የትግልም መነሽ ይህ መሆኑ ነው:: የነገድ የባሕል ጭቆና የለም ከማለት ይልቅ በኤርትራ ሕዝቦቸም ላይ ሆነ በሌሎቹ ባለው መንግሥት አማካይነት የአማራ ባሕል:የአብዛኛው አማራ ሃይማኖት/የክርስትና/በመንግሥቱ አፈቀላጤ ራዲዮም ሆነ በሌላም ድርጅት አማካይነት በሀይል በማስፋፋት የሚያደርገውን ጥረት አጥብቀን እንወግዛለን::ታሪክ እንዳሳየን እንደሚያሳየንም አንድ ገዥ ቤተሰብ የተወሰነ ብሔር/ናሺናሊቲ/አባል በመሆኑና በዚያ በብሔር አማካይነት ሥልጣን ስለሚይዝ:ጠበቃ ሆኖ የሚቆመው ለዚያው ብሔር ነው:: የዚሁንም ብሔር ባሕልና ወዘተ. ለማስፋፋት ይጥራል:: የሌሎቹን ባሕል ወዘተ ይጨቁናል ማለት ነው::

እሊህ ቲዎሬቲሻኖች በዚሁ ገጸ ለጠቀ እሉና እንዲህ ይላሉ: "ጭቆናና ገፍ የሚወርድበት የሃይማኖት ወይም የነገድ ልዩነት በመኖሩ ሳይሆን ዘራፊዎቹ በሥልጣን ላይ

በመወዛፋቸው ነው::" ለመሆኑ የምትጽፉትን ታውቃት ይሆን?
ታውቁታላችሁ እንጂ::ለይምሰል መንግሥትን አውግዛችሁ በሌ
ላ አቧያ እነሆ ሥርዐትን /መንግሥትን አላሰገም ሥርዐትን ነው
ያለነው:ልብ በሉት/ የሚያስከትላቸውን ማስከተል ያለበትን
ልዩልዩ ጥቆናዎች የለም ትሉናላችሁ::በማወናበድ መራቀቅ ይባ
ላል:እንዲህ ነው እንጃ::ከፉነቱ እውነት ሁልጊዜ አሸናፊ
መሆኑ ነው::እንድገመውና:ጥቆና መለኩ ብዙ ነው::የሃይማ
ኖትም የነገድም ሊሆን ይችላል:በኢትዮጵያ ይህ ሁናቴ ጎልቶ
ይታያል::

በዚሁ በገጽ 45 ስንመለከት: "በተለይ የኢትዮጵያ
ተጨቋኝ ሕዝቦችና ሬቮሉሽናዊ ኢትዮጵያውያን የኤርትራን ሕዝብ
መደገፍ "ሕብተግዴታቸው"ሲሆን በያለበት አቀር ቋጡንና ገፈና
ውን መንግሥት መቋምና ማጥቃት ደግሞ ዋና ተግባራቸው መሆኑን
እንዲገነዘቡት ያስፈልጋል::"

"የኤርትራን ሕዝብ መደገፍ"በምትሉበት ጊዜ የኤርትራን
ሕዝብ ትግል ማለታችሁ ይሆን?ትግል በውስጠ ታዋቂ መቅረቱ
ነው ማለት ነው::ወላዋይ አቋማችሁን ለመሸሸግ የማይሆነውን
ስትጽፉ መጣፍ ያለበትን ቃላት ስትሰርቁ /ችግሩ መቼ የቃላት
ጨዋታ ሆነ የአቋም ነው እንጂ::/

የኤርትራን ሕዝብ መደገፍ ሲባል ምን መባሉ ነው?
የኤርትራ ሕዝቦች ነጻነቴ ይሰጠኝ ባዮች ናቸው:: የብቻ መን
ግሥት ሳቋቁም ባዮች ናቸው::በዚህም ጥያቄ ሌኒን እን
ዲህ ይላል:: /ጥቀስ ከሌኒን/1)ይህንን ስነፍጥረታዊ
የብሔራዊ ንቅናቄ መነሻን ነው ሬቮሉሽናዊ ጓደች ተረዱተው:



1) ቁጥር ከተደረገቻው ገፅ 26-27 ተመልከት!

የኤርትራን የብቻ መንግሥት የማቋቋም መብት መደገፍ ያለባ
ቸው::

ከ1968 ዓም ጀምሮ የኤርትራ ሕዝቦች ትግል መደ
ገፍ እንዳለበት ማህበሩ ያመነበት ጉዳይ ነው::ሆኖም ያላ
መነበት የኤርትራ ሕዝቦች ጥያቄ ምንም ዓይነት ጥያቄ
ቢሆን:ሕዝቦቹ እስከሚደገፉት ድረስ መደገፍ እንደሚኖርብን
ነው::በዚህም ላይ የኤርትራ ሕዝቦች የብቻ መንግሥት ለማ
ቋቋም የሚያደርጉት ትግል:መደረግ ያለበት የታሪክ አደገት
መሆኑን መረዳት ይኖርብናል::ይህም ከሆነ ዘንዳ:የኤርትራ
ሕዝቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን መብት እንዳ
ላቸው:ይኸውም ከሌላው ግዛት እስከመገንጠል የሚደርስ ነው::
ከላይ የተጠቀሰውን ሁኔታ የማናምንበት ከሆነ:የነጋቢን ጀብ
መሆናችን ነውናራሳችንን ከሬቮሉሽናዊ ክልል እንሰርዘው::

በዚሁ ገጽ ቀጠል ያደርግና "ነጻነት ገፋፊ:ሰላም
አደፍራሽ:ሕዝብ አሳራዥ የሆነው የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት
ካልወደቀ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀን አይወጣለትምና::ገፋፊው
መንግሥታእንዲወድቅ ደግሞ ከያለበት በያለበት መመታት አለ
በትና::"ይላሉ::ጉድ ፈላ:የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጠላቶች
ፊውዳሊዝም /ማለት ስርዐቱ/ ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራት
ካፒታሊዝም መሆኑ ቀርቶ የንጉሠ ነገሥት መንግሥቱ ሆነ!
የናንተ ነገር በዚሁ ያከትማል::ለማንኛውም ታሪክ ያፋር
ደናል::ደግሞስ የሕዝቦችን ትግል በተለይም የኤርትራን
ትግል የምትደግፉት ለኤርትራ ሕዝቦች በማሰብ መሆኑ ቀርቶ
የመንግሥቱን መውደቅ ስለሚያስከትል ነው ይባላል?ታሪክ
ይፈርደዋል::የኤርትራን ሕዝቦች ትግል መደገፍ ያለበን

የምንደግፈውም መንግሥትን ስለሚያደክም አይደለም፡፡ ለኤርትራ ሕዝቦች ባለን ድጋፍ ላይ ተመርኩዘን ነው እንጂ፡፡ ብንወድም ባንወድም የኤርትራ ሕዝብ ትግል መንግሥትን ያደክማልና፡፡

እንግዲህ በኤርትራ ሥርዐቱ በካፒታሊዝም በመተካት ላይ ከሆነ ከዚህ ከካፒታሊዝም መምጣት ጋር የሚፈጠረው ሕብረተሰብ "ኔሽን" የሚባለው ሆኖ እናገኛለን፡፡

ኔሽን ማለት ከረዥም ታሪካዊ ሁኔታ በኋላ የሚወለድ ግንኙነቱ ጠንካራ የሆነ ሕብረተሰብ ሲሆን፡ይህም ሕብረተሰብ 1/ በኢኮኖሚ የተሳሰረ 2/በአጠቃላይ ግዛት ውስጥ የሚኖር 3/አንድ አጠቃላይ ቋንቋ ያለው 4/ሳይኮሎጂካዊ አቀራረጽ /ብሄራዊ ባሕሉ/ አንድ የሆነ ሕብረተሰብ ማለት ነው፡፡

ለማጠቃለል፡በኤርትራ ባሁኑ ጊዜ ያሉት ሕብረተሰቦች ኔሽን ተብሎ የሚጠራውና ብሄር /ናሽናሊቲ/ ተብሎ የሚጠራው በባላባት ስነሥርዐት ውስጥ የሚወለዱት ሕብረተሰቦች ናቸው፡፡ ይህም ከሆነ የኤርትራ ሕዝቦች ነገድ አይባሉም ማለት ነው፡፡

"የአንድ ነገድ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን መብቱ ሲረጋገጥለትና በነገዶች መካከል እኩልነት ያለምንም እንቅፋት ሲረጋገጥ፡" ተሳሳችሁ መሰል፡፡አቋማችሁ ትክክል መስሎ ቢታይም የራስን እድል በራስ መወሰን የባሕል እኩልነት ሲጸድቅ ብቻ መሆኑ ነው መሰል የናንተ አስተሳሰብ፡፡ግማሽለብ ሬቮሉሽነሪ የሚያስበላችሁ ይህ ነው፡፡ ቁርጣችሁ ቁራርጣችሁ ጣእሙን አሳጥታችሁ በተፈረና ስትቸሩ የጻፋችሁት ሕዝባዊ ቲዎሪ ለማወናበድ እመቴ መስሎ ታይታችሁ እንደሆነ፡ "ቤቱ



ፈርሶአል፡ዳቦው ተቆርሶአል እንላችኋለን፡፡" በለአንድ ኔሽን የራሱን በራሱ የመወሰን መብት አስታሊን እንዲህ ይላል፡ /ጥቀስ ከእስታሊን/2) የአንድነታችን ምንጭ የባሕል እኩልነት ሲኖር ነው ብትሉም ሌኒን እንዲህ ይላል፡ / ጥቀስ ከሌኒን/3)

በገጽ 47 እንዲህ ይላል፡ "የአንድነታችን ዋስትናመግባባት መፈላለግና መልካም ፈቃድ እንጂ ሀይል ሊሆን አይገባውም፡፡ /ደህና ብላችኋል፡፡/ ነገር ግን መረሳት የሌለበት ቁም ነገር ተበዝባዦች ነጻነታቸውን ለማግኘት የትግል አንድነት እንደሚያስፈልጋቸው ነው፡፡

የትግል አንድነት ያስፈልጋል በምትሉበት ወቅት፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባንድነት ተነስቶ ይዋጋ ነውን? ቀደም ብሎ ትግሉን የጀመረው ሌላውን ግዛት ይጠብቀው ለማለት ነውን? ነውስ ከበርቴ ምሁራን ምን ለማለት ነው የፈለጋችሁት?

ለማንኛውም፡ ማንኛውም ቀን ሬቮሉሽነሪ ለሕዝቦች አንድነት የሚጥር ነው፡፡ትግሉም በአንድነት ለማቀናበር ሁኔታው የሚፈቅድ ከሆነ፡ሊደከምበት የሚገባ ነው፡፡ግን በማንኛውም ሁኔታና ሁልጊዜ ትግሉ በአንድነት ይራመድ ብለን አንልም፡፡የሶሽኢኮኖሚክ ግንኙነት ከቦታ ወደቦታ ይለያያልና የጭቆናው ጥልቀት ከቦታ ቦታ ይለያያልና፡፡ በኢትዮጵያ ያሉ ጭቁን ሕዝብ እለ ለማለት አይደለም፡፡ግን የጭቆናው ደረጃ መለያየቱን ለመጠቆም ነው እንጂ፡፡ ተጨቋኝ ኔሽኖች ወይም ብሔሮች ከጨቋኝ

ብሄር ወይም ነገድ በበለጠ ስለሚጨቆኑ /በቋንቋ በሀል ወዘተ/ ትግሉን ቀደም ብለው ለመጀመር ይችላሉ::

በዚሁ ገጽ ስለዚህም የተቀረተ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የኤርትራን ሕዝብ /ሕዝቦች እንበለው/ ትግል እንዲደግፉት: በጨቋኙ ሥርዐት ላይ ስቓቸውን እንስተው ከወንደሉ እንዲታገዱ እንዲያደርጉ አስቸኳይ ጥሪ ይደረግላቸዋል። ዱንቋ አስቸኳይ ጥሪ::እንደዚህ ዓይነቱ ጥሪ የምኞት ጥሪ መሆኑን ሳትረዱ ቀርታችሁ ይሆን?በታስቡትስ ምሁራን እናንተ ራባችሁ ይህን የኤርትራ ጥያቄ ነፋስ የነካው ገለባ በምታደርጉበት ጊዜ:ጥያቄውንም በተከከለኛው መንገድ ለመረዳት ሳትጥሩ:የሕዝቡን የቀደሞ አቋሙን ቀንጣት እንኳ ሳትቀይሩ:ምን ሲደረግ ነው ይህን የምኞት ጥሪያችሁን ሰው እንዲቀበል የምትጥሩት? ተወናብዳችሁ ለማወናበድ አትሞክሩ::

እኒህ ንዑስከበርቴ ምሁራን በዚች በስስት ገጽ ስራቸው የተቻለውን ያህል ለመዘላበድና ለማወናበድ ሞክረዋል: ሰፋ አርገው በጻፉ ኖሮ ንዑስ አቋማቸውን በበለጠ ለማሳየት በሞከርን ነበር::

በበራቸው ውስጥ ማንኛውንም ቀን ሬቮሉሽነሪ የሚያሳዝነው ነገር ቢኖር:የኤርትራን ሕዝቦች ትግል የሚመራው: የኤርትራ ሕዝቦች አካል:ፋላጭ የትግል አቀነባሪ የሆነው የኤርትራ ግንባርን ባንዲት አረፍተነገር እንኳ ሳይገልጹት መቅረታቸው ነው::አንድ እውነት አለ::ይኸውም የኤርትራ ነጻ አውጭ ግንባር አቀጣጫውን ከጊዜ ወደጊዜ እያሻሻለ ትግሉን መምራቱ ሲሆን: በአጭሩ ለመናገር የኤርትራ ግንባር መኖሩ ነው:: የኤርትራ ሕዝቦች ትግል እንስተን የኤርትራን ነጻ አውጭ ግንባር የማናነሳበት ምንም ምክንያት የለም::



የሕዝቡ አካል ነው ብለን እናምናለን::

ለማጠቃለል:በኤርትራ ባሁኑ ጊዜ የሚካሄደው ትግል መነሻው ትክክለኛ የታሪካዊ ውጤት በመሆኑ ንቅናቄውን መደገፍ ይኖርብናል::ይኸውም ንቅናቄ የራሱን መንግሥት ለማቋቋም ጥረት ያደርጋል::ይህንንም ታሪክ ይደግፈዋል::ማንኛውንም የብሄራዊ ንቅናቄ ታሪክ የሚደግፈው መሆኑን ተረድቶ ለምን እንደሚደግፈው ሌኒን እንዲህ ይላል: /ጥቀስ ከሌኒን/4

## ጊዜያዊ ችግሮችና የጊዜው ጥያቄ

ማንኛውም ፕሮግራም ያለው ንቅናቄ /በኛም አንጻር የተማሪው መሆኑ ነው/ ምንም ነገር ለማከናወን በሚያቅዱበት ወቅት:አስቀድሞ የጊዜው ጥያቄ ምንድን ነው ብሎ መጠየቅ ግድ ይኖርበታል:: የኤርትራ ብሄራዊ ንቅናቄና የኤርትራ ተማሪዎች ማህበር የጊዜው ጥያቄ ነው ብለን እንገምታለን::

በኤርትራ ስላለው ትግል መለስ እንበልና ይህ ትግል የሚካሄደው በሰው ፈቃድ ሳይሆን በሃገሪቱ ውስጥ በሚገኘው ሰሸ ኢኮኖሚክ ግንኙነት ነው::በኤርትራ ችግሩ በዘበዛው ጭቆናው እያደገ በመሄዱ እስከጠበንጃ ትግል የሚመራ ድርጅት ሊቋቋም ችሉአል::

የኤርትራ ተማሪዎች ማህበር መቋቋም ከዚህ ዝርዝር የማይጨጣ ሆኖ እናገኘዋለን::ይህም ማህበር ታሪክ ሊወልደው የሚገባ የታሪክ ልጅ ነው::በሌላም አባባል ይህ ማህበር ጭቆና የወለደው ከሆነ: በውስጡ ዴሞክራቲክ ንጥረነገሮች

ይገኙበታል::ይህም ስለሆነ ለዚህ ማህበር ሙሉ ድጋፍ ይሰ
ጠዋል::ሕገማህበሩን ማወቁና አለማወቁ ሁለተኛ ማለትም
/ሰከንደሪ/ ጥያቄ ነው::ሕገማህበሩን ማወቁ የሚረዳው በት
ግሉ መቀናበር ውስጥ ያሉ ስህተቶችን በነቀፋ መልክ እንዲ
ለማውገዝ እንዳልሆነ የሚባት ነገር አይደለም::

በኤርትራና በሌሎቹ ደቡባዊ ግዛቶች የተለያየ የትግል
ደረጃ ይታያል::በኤርትራ ትግሉ ጠንከር ያለና በፖሊቲካ
ንቃት ራመድ ያለ ሆኖ ሲገኝ:በደቡባዊ ኢትዮጵያ ግዛቶች ትግ
ሉ ከዚህ ደረጃ አልደረሰም::የትግሉ ደረጃ ከተለያየ የት
ግሉ ተሳታፊዎች የተለያየ የትግል አቋምና ግብ ይኖራቸዋል
ማለት ነው::ይህም ስለሆነ ከነዚህ ልዩልዩ ቦታዎች የተገኙ
የትግል ተሳታፊዎች አንድና ተመሳሳይ ጠላት ቢኖራቸውም በግድ
ባንድነት ይሳተፋሉ የምንልበት ምክንያት ሊኖር አይቻልም::
ይህ ሊሆን የሚችለው ሪቮሉሽነሪ ማርክሲስት ሌኒኒስት የሆነ
ፓርቲ ተቋቁሞ ትግሉን እንደየቦታው ሶሽኢኮኖሚክ ሁኔታ እያየ
በሚመራበት ጊዜ ብቻ ነው::ትግሉን ለማቀናበር ፓርቲው የሚ
ገጥሙትን ችግሮች ተወት አድርገን ነው እንዲህም የምንለው::

በዚህም አንጻር የኤርትራ ተማሪዎች ተግባር ሆኖ
የሚገኘው አሁን ባለው ግንባር ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተ
ዘዋዋሪ ስህተቶቹንም ሆነ ጉድለቶቹን ማረምም ሆነ ማሙዋላት
ሲኖርባቸው:ሌላውን ሕብረተሰብ የሚወክል ጊዶ ድርጅት
የሚመረጥበትን ሁኔታ ያጠናል::ይህም የሚያሳየን ባሁኑ
ጊዜ የነዚህ የተማሪ ማህበሮች የራሳቸው የሆኑ በየይዘ
ታቸው ከሞላ ጎደል አንድ ቢሆኑም በዓይነታቸው የተለያዩ
ፕሮግራም እንዳላቸው ነው::ፕሮግራሙ የዓይነት ልዩነት



ካለው እነኚህ ህይሎች ማንኛውንም ስራ የግድ በአንድ ላይ
መስራት አይኖርባቸውም:: /ይህም አባባል ለዴሞክራቲክ ለሪቮ
ሉሽነሪዎች እንዳልሆነ ግልጽ እንዲሆን::/ ይኸም ከሆነ፣
ባሁኑ ጊዜ የኤርትራ ተማሪዎች ካለው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማ
ህበር መውጣታቸው /ባንዳንድ ቦታዎች መውጣታቸውን እናው
ቃለን/ ትክክለኛ የታሪክ ውጤት መሆኑን ካረጋገጥን በኋላ፣
ይህን ማህበር ማወቅ ግዴታችን መሆኑን እንረዳ::

ይህንንና ይህን የመሳሰሉ ተግባሮች ስንፈጽም ነው፣
ከኤርትራ ተማሪዎች ማህበርም ሆነ ከኤርትራ ግንባር ጋር የጠ
በቀ የትግል ግንኙነት ሊኖረን የሚቻለው::ይህም የጠበቀ ግን
ኙነት በሪቮሉሽነሪ ፓርቲ የሚመራ አጠቃላይ የሆነ የሕዝብ ግ
ንባር ለማቆም ይረዳል::ለብቻቸው መዘጋጀታቸውን መደገፍ
አጠቃላይ ግንባር ለመፍጠር ይረዳ ይሆናል በሚል መንፈስ ብቻ
ሳይሆን፣ዝግጅቱ ራሱ ትክክለኛና ስነፍጥረታዊ አቋም ነው ብለ
ን በማመን ነው::

ከላይ የተዘረዘረውን ምርኩዝ በማድረግ እነኚህ
ወረቀቶችን ጣፍን::እውነት ወይም ትክክለኛነት ቦታቸው ያለ
ተሰጣቸው ስለመሰለንና:ባሁኑ ጊዜ ይህ የተማሪ ማህበር እን
ኳ በፖሊቲካ ንቃት ከፍ ባለበት ወቅት:ግንባር ቀደም ሪቮሉ
ሽናሪ ፓርቲ የጊዜው ጥያቄ በሆነበት ወቅት:በማንኛውም ጊዜ
ያዊ ጥያቄ ላይ ትክክለኛና ሳይንሳዊ አገላለጥ እንደሚያስ
ፈልግ መረዳት ይኖርብናል::የኛም አቀራረብ በተማሪ ትግል ው
ስጥ መከፋፈልን /ፋክሺኒዝም/ ለመፍጠር አለመሆኑ ግልጽ
እንዲሆን::ጥረቱ በተወናበዱ ቲዎሬቲሻኖች የተወናበደ ቲዎሪ
ለማወናበድ ስለተጻፈ ትክክለኛውን አገላለጽ ባጭሩም ቢሆን

እናበርክት በሚል ዓላማ ነው::ትክክለኛውን ዓላማችንን ለመፈጸም በሚደረገው ጥረት የሚመጡ እንከኖች ጊዜያዊ ናቸው ብለን እንገምታለን::እውነት ታሸንፋለች ብለን እናምናለን::

ጽሁፉ በመጽሄታችን ላይ የመታተም እድል ያጋጥመው ይሆን ለማንኛውም እንዲታተም እንጠይቃለን::

---

## መልስ

ከዚህ በላይ የሠፈረው ሂስ /ክሪቲክ/ የተላከልን በስብየት ህብረት ከሚኖር ፋና ከሚባል 'ጓዱ' ነው::ምናልባት ፋና የጥቀል ስም ባይሆን አይቀርም ብለን እንገምታለን::ጽሑፉ የተዘጋጀው በህብረት ሥራ ይመስለናል::ለዚህ ጽሁፍ ረዘም ያለ ሀተታና ትንተና ብንመለስለት ደስ ባለን ነበር::ይሁን እንጂ ጊዜና ቦታ በለማይፈቀዱ ከዚህ በታች ባጭሩ ዋና ዋና መስለው ለታዩን ነጥቦች መልስ እናቀርባለን::ይህን ከማድረጋችን በፊት አንዲት ነገር ከዚህ ላይ ብናመለከት ደስ ይለናል:: ሂስ ማቀረብ ጥሩ ነገር ነው:መተራረም ማህበራችን ይበልጥ ወደፊት እንዲራመድና ለኢትዮጵያ ህዝቦች አገልግሎት እንዲውል ለማድረግ ይቻላል:: የፋና ጓዶች ሂሱን በማቀረባቸው ደስ ይለናል:ነገር ግን ቀጸል ማብዛትና መፍተት በማንኛውም መንገድ የቀረበውን ሂስ ያጠነክረዋል:ያዳብረዋል:እዉነተኛ ያደርገዋል ብለን እናምንም::እንዲያውም ከጉዳት በስተቀር የሚያመጣው ትርፍ አይታየንም::ጓዶች ይህን ነጥብ



ለወደፊት በሚገባ እንዲያስቡበት ተስፋ አለን::

ወደ ሂሱ እንመለስ::እንደሚመስለን የቀረቡትን ዋና ዋና ነጥቦች ከአራት ቦታ ለመከፈል ይቻላል:: ሀ/ለጓደቹ በትክክል ያልገቡዋቸው ነገሮች አሉ:: ለ/ጓደች አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ስህተት ለማግኘት ስለጓጉ ይመስለናል 'የተራቀቁባቸው' ነጥቦች አሉ:: ሐ/ባንዱ ነጥብ ላይ በተለይ ትክክለኛ ሂስ አቀርበዋል:: መ/ለኛ ለራሳችን ያልተጧሩ ጉዳዮችን አስፍረዋል::እነዚህን ነጥቦች ባጭሩ እንመልከት::

ሀ/ ለፋና ጓዶች በትክክል ያልገባቸው የሚመስለን የመጀመርያው ነጥብ ስለሃይማኖትና ስለነገድ ጭቆና ነው::የኢትዮጵያ መንግሥት የኤርትራን ህዝብ ትግል 'በሃይማኖትና በነገድ ልዩነት ላይ የተመሠረተ' ለማስመሰል ሞክሮአል ስንል ምን ማለታችን ነው እዚህ ላይ ግልጽ መሆን ያለበት የተመሠረተ የሚለው ቃል ነው::ታሪክ እንደሚያመለክተው የሃይማኖትና የነገድ ልዩነት የትግል ሰንደቅዓላማዎች:የትግል አይዲዮሎጂዎች:በዙውን ጊዜ ጨቋኝ መደቦች የሚጠቀሙባቸው የሰፊውን ህዝብ መሰብሰቢያ መሣርያዎች ናቸው እንጂ የትግል አንቀሣቃሽ ሀይሎች አይደሉም::የትግሉ አንቀሣቃሽ ሀይል የመደብ ጭቆና ነው::ማለት:ከሁሉም በፊት:የዘራፊንና የተዘራፊን ግንኙነት የሚወስነው የኢኮኖሚ ግንኙነት ነው::

የኢትዮጵያ መንግሥት 'እስላሞች ተነሡብን' 'ትግሬ ሊያጠፋን ነው'ሲል ለመሸሸግ የሚፈልገው የገዥውን መደብ ዘረፋና ጭቆና መሆኑን ማንኛውም የታሪክን አረማመዱ የተገነዘበ ሰው ሊረዳው ይችላል ብለን እንገምታለን::ደግሞም የዚህ ዓይነት ፕሮፓጋንዳ ስርዓቱን በሁለት በኩል የሚጠቀም

ይመስለዋል፡፡እንደና ክርስቲያንና አማራ የሆነውን ዜጋ በኔ
ሰንደቅዓላማ ሥር ይሰበሰብልናል ብሉ ያምናል፡፡በኤርትራውያን
የዘር ውስጥ መከፋፈልን ያስከትልልናል ብሉ ያምናል፡፡ይህን
ጸረህዝብ ፕሮፓጋንዳ ለመከላከል ሳይንሳዊ እውነትን ከፕሮፓ
ጋንዳው ፊት ማስቀደም ያስፈልጋል፡፡ይህም ማለት የሃይማኖትና
የነገድ ልዩነቶች የህዝብ ማወናበጃና መሰለፊያ ሰንደቅዓላማዎች
እንጂ የጭቆና መሠረት አለመሆናቸውን ማሳየት ነው፡፡መግለጫው
በመጀመርያ አንቀጹ ያሠፈረው ነጥብ ይህን እውነት ነው፡፡

ይህ ስለተባለ ግን የሃይማኖትና የነገድ ጭቆና በኢትዮጵ
ያ የለም ማለት አይደለም፡፡መግለጫው የዚህ ዓይነት ጭቆና የ
ለም አይልም፡፡የፋና ጓዶች እንዳሉት ሁሉ ይህ "ድርብ ድርብ
ርብ"ጭቆና ነው፡፡የመደብን ጭቆና ተከትሎ የመጣ ነገር ነው፡፡
የዋናው ጭቆና ቀጥያ ነው እንጂ መሠረቱስ አይደለም፡፡የዚህ
ዓይነቱ አቀራረብ የፋናን ጓዶች እንዴት ገራ ሊያገባቸው
እንደቻለ አይታየንም፡፡

መሠረታዊ ሆነው ኢኮኖሚያዊ ጭቆና ተደራቢ ለሆኑት
የሃይማኖት፡የባህል፡የቋንቋ ጭቆናዎች·ተክክለኛ ቦታቸውን
መስጠት ያስፈልጋል፡፡በቲዎሪ ብቻ ሳይሆን በግብርም፡፡የዚ
ህ ዓይነቱ አስተሳሰብ በትክክል ካልገባቸው ሬቮሉሽናውያን
እንዴት አድርገው ነው እስላሙንና ክርስቲያኑን፡አማራውንና
ትግሬውን፡ወዘተ፡ ባንድነት ሊያሰልፉ የሚችሉት? ይህን ለማድረግ
ካልተቻለ የመደብ ትግሉ የት ላይ ነው? የፋና ጓዶች ይህን
ጉዳይ በሚገባ እንዳልተረዱት ጽሁፋቸው ያሳያል፡፡ "የኤርትራ
ህዝቦች ሃይማኖታችን፡ባህላችን ይከበር" "ለሃይማኖታችን ለባ
ህላችንእንዋጋለን" ይላሉ ብለው ጽፈዋል፡፡የኤርትራ ህዝብ፡
ወይም የኢትዮጵያ መንግሥት እንደሚጠራቸው፡"ሽፍቶች"ለሃይማኖት



ይዋጋሉ ሲባል የሰማነው ከኢትዮጵያ መንግሥት ፕሮፓጋንዳ ነው፡፡
በኛ አስተያየት የኤርትራ ህዝቦች የተነሱት ለዚህ አይደለም፡፡
እንደገና እናስታውስ፡በኤርትራ ህዝቦች ላይ የሃይማኖትና የባህል
ጭቆናዎች አልተደረጉም ማለታችን አይደለም፡፡ይሁንና አንድ ሃይ
ማኖት አንድ ባህል በሌለበት አገር ኤርትራውያን እንዴት ለሃይማ
ኖታችን ለባህላችን እንዋጋለን ሊሉ ይችላሉ? ምንም እንኳን የኤ
ርትራ ትግል አመራር እስካሁን ድረስ የተጣራ ፕሮግራም ባያወጣ
ለብሄራዊ ነጻነት የሚዋጋ መሆኑን ደጋግሞ ገልጦአል፡፡ባይገልጥም
ኖሮ ይህንን ለመገመት በተቻለ ነበር፡፡በዚህ ሁኔታ የፋና ጓዶች
የኤርትራ ህዝቦች ለሃይማኖታቸውና ለባህላቸው ይዋጋሉ ሲሉ የሀይ
ለሥላሴ መንግሥት የሚለውን አጸደቁለት ማለት ነው፡፡

ሁለተኛ ለፋና ጓዶች በትክክል ያልታያቸው ነጥብ በለትግል
አንድነት የሚናገረው ይመስለናል፡፡የትግል አንድነት ያስፈልጋል
ስንል የተጨቆኑ የኢትዮጵያ ህዝቦች ሁሉ መደጋገፍ አለባቸው ማለ
ታችን ነው፡፡አንድነት የሚለውን ቃል ከብዙ ዓመታት ጀምሮ በመ
ጽሄታችንና በየስብሰባችን ስንጠቀምበት ቆይተናል፡ይህም ቃል
ሶሊዳሪቲ የሚለውን የፈረንጅ ቃል የሚተረጉምልን ነው፡፡ለምሳሌ
ከቪዬትናም ህዝብ ጋር አንድነታችንን እንገልጻለን ስንል ሶሊ
ዳሪቲያችንን እንገልጻለን ማለታችን ነው፡፡እዚህም ላይ የተጠ
ቀምንበትበዚህ ትርጉም መሆኑን መጽሄታችንን የሚያነቡ ሁሉ
በቀላሉ የሚረዱት ይመስለናል፡፡የትግል አንድነት ያስፈልጋል
ስንል የኢትዮጵያ ህዝቦች ሁሉ ባንድ ጊዜና በያለበት ባንድነት
መነሣት አለባቸው ማለት አይደለም፡፡የህብረተሰብን ሳይንስ
ህሁ አሁን ገና በመቁጠር ላይ የምንገኝ ብንሆንም የዚህ ዓይ
ነቱን ቀዝታም አስተሳሰብ እና ቀርባለን ብሎ መገመት የሚቻል
አይመስለንም፡፡

የኢትዮጵያ ህዝቦች የኤርትራን ህዝቦች መደገፍ አለባቸው፡

በያሉበት ትግላቸውን ማፋፋም አለባቸው፡ለዚህም "ጥሪ እናደር
ግላቸዋለን"ስላለን የፋና ጓደኞች ያሸሙር መዓት አወረዱብን::
በኛ አስተያየት የባሌ ህዝብ፡የኦጋዴን ህዝብ፡የወለጋ፡የጎጃም፡
የሌላውም ክፍል ህዝብ፡እንዲሁም የኢትዮጵያ ተማሪዎች፡በያሉበት
ትግላቸውን ቢያፋፍሙ፡ይህ ራሱ ለኤርትራ ህዝቦች ትግል ትልቅ
ድጋፍና እርዳታ ነው:: የትግል አንድነትን በግብር መመሥረት
ነው::ታዲያ ይህ ስህተተኛ አስተሳሰብ ነው ወይ? ለ"ጥሪው"
የሆነ እንደሆነ፡ መጽሄታችን ለሰፊው ህዝብ በገፍ እንደማይ
ዳረስ እንገነዘባለን፡ንግ ገናለገና ጥሪያችን አይደርስልንም
ብለን ዝም እንበል?

በነገራችን ላይ፡በቴክኒካዊ ችግር ምክንያት አላተም
ንላቸውም እንጂ፡የፋና ጓደኞች ሌኒንና ስታሊንም ስለህዝቦች
መብት ከጻፉት ደጋግመው የእንግሊዝኛ ጥቅሶች አስፍረዋል::
ህዝቦች የራሳቸውን እድል እነሱ ራሳቸው ብቻ ለመወሰን መብት
እንዳላቸውና ሬቮሉሽናውያን ለዚህ መብት መታገል እንዳለባቸው
ሌኒን ያስተምረናል:: ነገር ግን የሌኒን ትምህርት በዚህ አያ
ቆምም::ለዚህ መብት በምንታገልበት ወቅት ለላብአደሩ አንድ
ነትም መታገል ግዴታችን መሆኑን ያስተምረናል::ባጭሩ የሬቮ
ሉሽናውያን ተግባር ጥምራ ነው፡ለህዝቦች ሙሉ መብትና ለላብ
አደሩ አንድነት መታገል::መግለጫው ሊያስተላልፍ የፈለገው
መልእክት ይህን ነው::አሁን ባለንበት ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝ
ቦች የትግል አንድነትን ይመሠርታሉ::ወደፊት ደግሞ እውነተኛ
የላብአደሩን መደብ አንድነት ሳይመሠርቱ እንደማይቀሩ እናም
ናለን::ለዚህም እንታገላለን::አቋማችን ይህ ነው::

ለ/ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው ነጥቦች ለፋና ጓደኞች
በትክክል አልታያቸው ብለን እንገምታለን::ይህ እንኳን በውነቱ



በክርክር ሊጣራ የሚችል ነገር ነው::ግን ጓደቹ ከዚህም ያለ
ፋና አንዳንድ የመራቀቅ፡የጠጉር መፍለጥ ፍላጐት ያሳያሉ የም
ንልበት ቦታ አለ::"የኤርትራን ህዝብ ትግል" በማለት ፈንታ
"የኤርትራን ህዝብ" ማለታችን ባንግላቸው ውስጥ ጥርጣሬን
አሳድሮአል? ግን መግለጫውን በሚገባ ቢያነቡት ኖሮ "የኤርት
ራ ህዝብ ትግል" የሚለው ስምንት ጊዜ እንደተጠቀሰ ለማየት
በቻሉ ነበር::ፊውዳሊዝም፡ኢምፔሪያሊዝም በማለት ፈንታ "የን
ጉሠ ነገሥት መንግሥት"/ቢተረጐም ኢምፓየር እስቴት የሚሆነው
ን/ ስለተባለ ተቀይመዋል::ከብዙ ዓመታት ጀምሮ መጽሄቶቻቸ
ን የሚያነቡ ሁሉ የንጉሠ ነገሥት መንግሥቱ ይውደቅ ስንል
ምን ማለታችን እንደሆነ ያውቃሉ ስንል እናምናለን::ሥርዐቱ
ይጥፋ፡ህዝባዊ መንግሥት ይቋቋም ማለታችን መሆኑን የማህበሮቻ
ችንን ፖሊቲካዊ አቋም የሚያውቁት ሁሉ ይገነዘቡታል::በተጨማ
ሪ መግለጫው ራሱ ስለጨቋኙ ሥርዐት፡ስለንጉሠነገሥቱ አገዛዝ፡
ስለፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት አቋም ይናገራል::በመደም
ደሚያውም አድሃሪው የንጉሠ ነገሥት አገዛዝና ጠባቂው ኢምፔ
ሪያሊዝም ይሸነፋሉ ይላል::በዚህ ሁኔታ፡የወጣው መግለጫ ከብ
ዙ ዓመታት ጀምሮ የጸደቀውን የማህበሮቻችንን ፖሊቲካዊ አቋ
ም ባንድአፍታ በመቀልበስ፡መግለጫው የሚጠይቀው የመንግሥቱን
/ጋቨርንመንት/ መለወጥ ተብሎ ሊጠረጠር ነውን በነዚህ በመራ
ቀቅ ነጥቦች ላይ ጊዜ ካጠፋን እንደፋና ጓደኞች ጠጉርን መፍ
ለጥ ይሆንብናልና ወደሚቀጥሉት ነጥቦች እንለፍ::

ሐ/ በፋና ጽሁፎች ውስጥ አንድ ጠቃሚ ሂስ አለ ለማ
ለት ቢቻል መብራራት ነበረበት የሚለው ነው::ምንም እንኳ
ባንድ መግለጫ /ያቋም መውሰጃ/ ውስጥ ብዙ ነገሮችን ለማ
ብራራት ባይቻል፡ነገድ፡ህዝብ፡ህዝቦች ወዘተ. ስንል በርግጥም
ምን ማለታችን እንደሆነ መብራራት ነበረበት::ይህ ትክክለኛ

ሂስ ነው::ይሁን እንጂ አንድ መታወስ ያለበት ነገር አለ:: ዓለምአቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር "ህዝቦች የወደፊት እድላቸውን የመወሰን መብት አላቸው" የሚለውን ሬሾሉሽና ዊ ኢቷም በግልጽና እንደሚመስለንም በማያሻማ ቋንቋ ሲወስድ የመጀመርያ ጊዜው ነው::በመግለጫው እንዲህ የሚል አለ: "እያንዳንዱ ህዝብ የወደፊት እድሉን እርሱ ራሱ ብቻ ለመወሰን መብት እንዳለው ማህበሩ ያምናል::"

ይህ ግልጽና የማያሻማ ነው ብለን እናምናለን::ስለቃሳት አመራረጥና ስለትርጉም የሆነእንደሆነ ግን ወደፊት በውይይትና በክርክር የሚጣራ ነገር ነው::ህዝብ ስንል ወይም ነገድ:አገር:ብሄር ምን ማለት እንደሆነ ወደፊት በህብረት መወሰን አለብን::

መ/ ከፋና ጽሁፍ ውስጥ ያልተጣሩ ጉዳዮች አሉ::ባንድ በኩል "የኤርትራ ግንባርን"ባለመጥቀሳችን ተቀይመዋል::እና የምናውቀው የሚከተለውን ነው::ከጥቂት ዓመታት በፊት የኤርትራ ነጻአውጭ ግንባር /ኢ ኤል ኤፍ/ድርጅት ጋር ማህበሮቻችን አንዳንድ ውይይት ጀምረው እንደነበረ ይታወሳል:: በ1969 አጋማሽ ላይ ይህ አመራር ተሸሮ በሌላ ተተከቶአል የሚል ዜና ደርሶን ነበር::ባሁኑ ጊዜ እንደምንሰማው ከሆነ ሁለት ድርጅቶች ያሉ ይመስለናል: የኤርትራ ነጻአውጭ ግንባርና የኤርትራ ህዝብ ነጻአውጭ ግንባር::በዚህ ባልተጣራ ሁኔታ ያንዱን ሆነ የሌላውን አመራር ስም መጥቀሱ ተገቢ መስሎ አልታየንም::ለማንኛውም ዋናው ነገር የኤርትራን ህዝቦች የነጻነት ትግል መደገፍ ስለሆነ በዚሁ ተወስነናል::የፋና ጓዶች ስለአመራሩ ይበልጥ የተጣራ ዜና ካላቸው ይላኩልንና በዚሁ ላይ



ተመሥርተን ወደፊት ይህን "ጉድለት"ለማቃናት እንደምንችል እንተማመናለን::

በሌላ በኩል ደግሞ የፋና ጓዶች ስለኤርትራ ተማሪዎች ማህበር ይጠቅሳሉ:: "ይህን ማህበር ማወቅ ግዴታችን መሆኑን እንረዳ"ይላሉ::መግለጫው በወጣበት ወቅት ስለተባለው ማህበር ከጭምጭምታ በስተቀር የሰማነው ነገር አልነበረም:የለም::በጭምጭምታ ተመርኩዘን እርምጃ መውሰድ አንፈቅድም::የኤርትራ ተማሪዎች ማህበርን በማወጅ ከማህበሩ በግልጽ ከተጻፈለት ዓለምአቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ስለማወቁ ጉዳይ ከኤርትራ ተማሪዎች ማህበር ጋር ውይይት /ዲያሎግ/ የማይጀምርበት ምንም ምክንያት የለም::በዚህ ረገድ በኢጣሊያን አገር የሚገኘ የኤርትራ ተማሪዎች ማህበር ከኤውሮፓው ማህበራችን ጋር በቅርቡ ግንኙነት ማድረጉን እዚህ ላይ እናስታውስ::

የፋና ጓዶች በጽሁፋቸው ውስጥ "እኒህ ንዑስከበርቴ ምሁራን በዚች በስስት ገጽ ሥራቸው የተቻለውን ያህል ለመዘላበድና ለማወናበድ ሞክረዋል" ሲሉ ዘልፈውናል::ቀጥሎም "ሰፋ አድርገው በጻፉ ኖሮ ንጹህ አቋማቸውን በበለጠ ለማሳየት በሞከርን ነበር" እያሉ ፎክረዋል::ንጹህ አቋማችንን ከዚህ በፊት በጽሁፎቻችን ደጋግመን አስታውቀናል: አሁን ያሰፈርነው ይህንኑ የሚያጸና ነው::ስለዚህ የኛን"ንጹህ አቋም" ለማሳየት ፋና ከንገዲህ መድከም እንደማይኖርበት እናምናለን::

ይህን ጽሁፍ ከመደምደማችን በፊት ለነቃት አንባቢዎቻችን አንድ ነገር ብናስታውስ ደስ ይለናል:: ባሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ብሄሮች /ኔሽንስ ወይም ናሺናሊቲስ/ ጉዳይ እንደኛው ዋናው የማህበራችን ጥያቄ ሆኖአል::ይህን ጥያቄ በሚም

ለከተው በኰል፡በማህበሮቻችን ውስጥ ባሁኑ ወቀት አምስት ዓይ
ነት ያህል ሰዎችን ለመለየት ይቻላል ብለን እንገምታለን፡፡

ሀ/ የብ ሄሮች ጥያቄ ገብ ቷቸው የሚቃወሙ፡አርግጠኛ የቀኝ /አድሀሪ/ ትምክህተኞች /ማለት ሾቪኒስቶች/ አንድነታችን ለመጠበቅ ከፈለግን ለመገንጠል የሚነሣው በሀይል መጨፍጨፍ አለበት የሚሉ ፋሺስታዊ አቋም ያላቸው፡፡ ለ/ ጥያቄው ሳይገባቸው ከፊውዳሉ ሥርዐት ትምህርት በቀሰሙት ኢትዮጵያዊ በሚያስኙ ትምክህት ብቻ የፀኑ፡፡ ሐ/ሳያውቁ ጠባብ ናሺናሊስቶች የሆኑ የወገናቸው መዘረፍና መጨቆን ብቻ የሚታያቸው ቀደም ተራይባሊስት ይባሉ የነበሩት፡፡ መ/ የገራ /ሬቮሉሽናውያን/ መስለው በርግጥ ግን ጠባብ ናሺናሊስት የሆኑ፡፡ ሠ/ ጥያቄው ገብ ቷቸው ለብ ሄሮች ሙሉ መብትና ለሳብአደራ መደብ አንድነት ለመ ታገል በርግጥ የሚፈልጉ፡፡

ባሁኑ ወቀት እነዚህ አቋሞች በማህበሮቻችን ውስጥ ጕንለጕን ይገኛሉ ብለን እንገምታለን፡፡ያቋሙ መብዛትና መዘረከረከም የጊዜው ምልክት ነው፡፡በዚህ ሁኔታ ቀን ሬቮሉሽናዊ ሁሉ በትእግሥትና በብርታት መታገል ይኖርበታል፡፡

---



<u>ትንሽ ተጨማሪ</u>

በነገራችን ላይ፡"ክርስቲያን ሳይንስ ሞኒተር" የተባለው ያሜሪካን ጋዜጣ በማርች 28/1969 ከዚህ በታች ያሠፈር ነውን ዜና ጽፎ ነበር፡፡እና እስከምናውቀው ድረስ ከዚህ በታች ያለውን የሚናገረው ኦስማን ሳላህ ሳቤ አሁንም ይኤርትራ ግንባር መሪ ነው፡፡ ሌላ ሀተታ ሳንጨምር እነሆ ዜናውን እና ቀርባለን/

Mr. Sabbe said he had spoken recently with the United States defense attaché in Mogadishu, Somalia, about Chinese Communist arms aid to the ELF.

Mr. Sabbe said he explained that "the Chinese People's Republic gives us military aid. But th ere is no Communist tendency in the ELF program, though we have some individuals who think along Communist lines...."

Mr. Sabbe was asked how the ELF feels about the large United States military radio-relay and monitoring station outside Asmara. He replied, "We have said before and we repeat that we are not against the Americans or their interests in Eritrea....

"We have never damaged American interests in Eritrea. We never intend to do so as long as United States forces in Eritrea remain neutral"

1. ...the tendency of every national movement is towards the formation of national states under which these requirements of modern capitalism are best satisfied.....
...Consequently, if we want to grasp the meaning of self-determination of nations, not by juggling with legal definitions, or "inventing" abstract definitions, but by examining the historico-economic conditions of the national movements, we must inevitably reach the conclusion that the self-determination of nations means the political separation of these nations from alien national bodies, and the formation of an independent national state.

2. The right of self-determination means that only the nation itself has the right to determine its destiny, that no one has the right to forcibly interfere in the life of the nation, to destroy its schools and other institutions, to violate its habits and customs, to repress its language or curtail its rights.

The right of self-determination means that a nation may arrange its life in the way it wihes. It has the right to arrange its life on the basis of autonomy. It has the right to enter into federal relations with other nations. It has the right to complete secession. Nations are sovereign and all nations have equal rights.

3. Socialist parties which did not show by all their activity both now and during the revolution, and after the victory, that they would liberate the enslaved nations and build up relations with them on the basis of a free union - free union is a false phrase without the right to secede - these parties would be betraying socialism.



4 The right of nations to self-determination implies exclusively the right to independence in the political sense, the right to free political separation from the oppressor nation. Specifically, this demand for political democracy implies complete freedom to agitate for secession and for a referundum on secession by the seceding nation. This demand, therefore, is not the equivalent of a demand for separation, fragmentation and the formation of small states. It implies only a consistent expression of struggle against all national oppression The closer a democratic state system is to complete freedom to secede, the less frequent and less ardent will the desire for separation be in practice.

## ከህዝቡ ጋር መቀሃዱ የምንለው ይህ ነው::

ከጊኔ ቢሣው አርበኞች ጋር::

ከሬኔ ሰፍር

ለ ሞንዴ: ግንቦት 5/6 7: 1970

### 1/ ከሁኔታው ጋር የተሳሰረ ሬቮሉሽን

ቪክቶር የተባለው የጊኔና የካፑ ቬርዴ የነጻነት ፓርቲ አባል በፈገግታ ከዚህ ወዲያ ያለው አገር የኛ ነው በማለት ገለጸልን::ጥቂት ፋኖዎች እቃቸውን በመቀበል ወደማረፊያ ቦታ መሩን::ጓዞአችንን ወደደቡብ ለመቀጠል ጀንበር እስከትጠልቅ በመጠበቅ ነበርን::ሌሊቱን በሙሉ ስንጓዝ አደርን::ጊኔ ቢሣው ውስጥ ሰው ያለ ሃሳብ ካንዱ ቦታ ወደሌላ ለመጓዝ የሚቻለው በእግር ብቻ ነው:ያለበለዚያም የፖርቱጋል የጦር ጀልባዎችን የማያሳልፍ አነስተኛ ፈሳሽ ውሃ ካለ በታንኳ ለመጓዝ ይቻላል::ጫካው በሙሉ የአርበኞች ግዛት ነው::ህዝቡ ከጠላት አኤሮፕላኖች በደኑ እየተጋረደ በነጻ አውጭው ግንባር እየተደራጀ ከሰባት ዓመታት ጀምሮ የፖርቱጋልን የጦር ሀይል በጠበንጃ እየተቋቋመና ደግሞ ዱል በመምታት ባንዳንዱ ምሽጎችና ጦር ሠፈሮች እንዲሸሸግ ሲያስገድደው የገዢውም ሥልጣን ቢሳው ከተማና ምስራቅ ጊኔ ውስጥ ብቻ እንዲወሰን አድርጎታል::

ጊኔ ቢሣው ስፋቱ 3600 ኪሎሜትር ካሬ ሲሆን የሚገኘውም በሴኔጋልና በጊኔ ሬፑብሊክ መካከል አትላንቲክ ውቅ



ያኖስን ድንበር በማድረግ ነው::እኤአ ሚያዝያ 3 ቀን 1959 ህዝቡ ለመጀመርያ ጊዜ ተነሣ::ይህ አመጽ ባስከተለው 'በፒጂጊቲ አልቂት' በትንሹ ሃምሳ ሰው ተፈጀ::በዚህም ጊዜ የብሄራዊ አርበኞች ድርጅት የትግሉን አመራር ለመለወጥ ወሰነ::በግንቦት 19 ቀን 1959 የግንባሩ መምርያ ኮሚቴ ትግሉ:ከፖሊቲካ ትግል ወደጠበንጃ ትግል እንደተሸጋገረ አስታወቀ:: የፖርቱጋል የቀኝ አገዛዝ ህዝቡ ለነጻነቱ ያለውን የሚያደርገውን ጥረት ሁሉ በሃይል በመቃወሙና በአሚልካር ከብራል መሪነት ቁጥራቸው መጠነኛ የሆነ ብሄራዊ ተቀናቃኞች ከ1956 ጀምሮ ያደረጉት የፖሊቲካ ትግል ምንም ውጤት ባለመስጠቱ የጠበንጃ ትግል አስፈላጊነት ግልጽ ነበር::ይህ ሲሆን ከህዝቡ ከመቶው ዘጠናአምስቱ ገበሬ ነው ::ለጠበንጃ ትግል ተቀዳሚ ምሰሶ የሚሆነው ታጥቆ የሚነሳው ገበሬ ብቻ ነበር ማለት ነው። ስለዚህ የቀኝ አገዛዝን በቃል ከመኰነን ደረጃ አልፎ ሰፊውን ገበሬ ህዝብ ከብዙ ዓመታት ጀምሮ ተጭኖ የሚጨቁነና የሚበዘብዘውን ጠላቱን ማሳወቅና ምንም እንኳ ፈረንጁ ሆኖ የደረጀ ቢሆን በጦር ሀይል ነጭነቱን እንደያዘ ሊደመሰስ እንደሚቻል ማረጋገጥ ያስፈልግ ነበር::

### 99 ነጥብ 7 መሃይማን

የቀኝ አገዛዝ የተመሠረተው በንግድ ግንኙነት ላይ ነው::ገበሬው በሙሉ /በተለይ አራሺዱ/ ለፖርቱጋሎች የንግድ መደብሮች ይሸጣል::በመሬት ሥሪት ረገድ ምንም ችግር አልነበረም:ምክንያቱም በዘልማድ መሬት ምን ጊዜም ቢሆን የመንደሩ የጋራ ሃብት ነው::የፖርቱጋል የቀኝ አገዛዝ አስተዳደር በነዚህ :የርሻ ሥራዎች ላይ ከባድ ግብር ሲጥልባቸው በተጨማሪ ደግሞ ህዝቡን በሀይልና ያለደሞዝ በማሰራት ስራ የመገናኛ

መንገዶቸን ለመቀየስ ቻለ::ህዝቡን በድንቁርና ቀንበር
በማሠር /99 ነጥብ 7 ከህዝቡ ያልተማረ ሲሆን:ከ500
ዓመት የፖርቱጋል ቅኝ አገዛዝ በኋላ የዩኒቨርሲቲ ትም
ህርት የቀመሱ ያገር ተወላጆቸ 14 ብቻ ናቸው/ እንዳይነ
ቃና ባካባቢ አገሮቸ ከሚደረገው የፖሊቲካ ንቅናቄ እንዲ
ርቅ አድርጎታል::ከጐረቤት አፍሪካ አገሮቸ ጋር እንኳ
ሲተያይ የህዝቡ የጤና ደረጃ በጣም ዝቅ ያለ ነው::ከመቶ
ህጻናት ውስጥ በሳሳው አምስት ዓመት ሳይሞላቸው ይሞታሉ:
በካፑ ቬርዴ ደሴት ላይ ድርቀት በሚያስከትለው ረሃብና ቸ
ጋር ተቀጥሮ ከሚያርሰው ህዝብ በብዛት ይፈጃል::በ1959
ብቻ ከ10000 ህዝብ በላይ አልቋል::

አሚልካር ካብራል ይህን ሁኔታ በመመልከት ገበሬው
ህዝብ ተነቃንቆ ጠበንጃ ይዞ የሚያስለፈው ከጉያው የተመለ
መሉ ተቀናቃኞቸ ህዝቡ በሚገባው ቀላል ቋንቋና አለታዊ
ኑሮውና ቸግሩ ላይ በተመሠረተ ማስረጃዎቸ የቅኝ ግዛት
የሚያስከትልበትን ገፍና ጭቆና ሲያስረዱት ሲቻሉ
መሆኑን ተገነዘበ::ሶስት ዓመት ሙሉ የግንባሩ ተቀናቃ
ኞቸ በዱር በደኑ በመሠማራት ከቆዩ በኋላ በ1963 ዓም
ድርጅቱ ለባላገሩ ለማድረስ የፈለገውን የፖሊቲካ ትምህርት
በሚበቃ እንዳጠናቀቀ አመነ:: "ገበሬውን ለማስነባትና
ድጋፉን ለማግኘት በቻይና ሪቮሉሽን ወቅት እንደታየው
ሁሉ ቀላል ሆኖ አላገኘነውም::ብዙ ጥረትና ጊዜ ወስደ
ብናል::" እንዲህ ዓይነቱ ያመራር አቀድ ከሁለት ዓመት
የደፈጣ ጦርነት በኋላ ግ:ባሩ የአገሪቱን ሁለት ሶስተኛ
ነጻ ለማውጣት እንዲቻል አድርጎታል::

<u>ማህበራዊ አመራር</u>



አሚልካር ካብራል በርሻ መሃንዲስነት ባንድ ተልቀ
የፖርቱጋል ኩባንያ ውስጥ ሲሰራ በነበረበት ጊዜ አገሩን ከ
ዳር እስከዳር እየዞረ ለማየት ቻሎአል::የህዝቡን ባህል:የልዩ
ልዩ ነገዶቸን የአስተዳደር ልምድ ባላንተ ከተባሉ"አረመኔ"
ሕዝብ ህብረተሰብ እስከ ፉላ እስላሞቸ ባላባታዊ አቋም ድረስ
እየተዘዋወረ ለመመርመር በቅቷል::በነዚህ ልዩልዩ አቋሞቸ ው
ስጥ የፖርቱጋል ባእድ የቅኝ ግዛት አስተዳደር ያስከተለውን
ለውጥ ተመልክቶ አጥንቷል::

የነጻ አውጭው ግንባር ርእዩተ ዓለም የተመሠረተው
የአገሪቱን ጊዜያዊ ሁኔታ በመመርኰዝ ተጨባጭና በሥራ ላይ
ሊውል በሚቻል የፖሊቲካና የኢኮኖሚ ፕሮግራም ላይ ነው::
የፖሊቲካ ካድሮቸ ከሶብየት ሕብረት:ከሕዝባዊ ቻይና ወይም
ከኩባ ሪቮሉሽናዊ አድገት ይልቅ የባእድ ቀንበር በአገሪቱ
ላይ ያስከተላቸውን ጠንቀቸና የትግሉ ድርጅት በወጠነው አቀድ
መሠረት የሕዝቡ የእለት ቸግር እንዴት ሊፈታ እንደሚቻል ማስ
ረዳትና ማብራራቱ ይቀላቸዋል::የጊኒ ቢሣውን የትግል ንቅናቄ
ዓይነታዊ የሚያደርገው ከሁኔታው ጋር የተያያዘ መሆኑና ከተራቀቀ
የቴዎሪ ትቸት የራቀ መሆኑ ነው::

የጊኒና የካፕቬርዱ የነጻነት ግንባር ከሁለት አን
ቀፋቶቸ ሊያመልጥ ቻሏል::የአሚልካር ካብራል ትክክለኛ አመራር
ፓርቲውን ከመሠረተበት ጊዜ አንሥቶ ዋና ጸሐፊ ሆኖ እስካለ
በት ጊዜ ድረስ ለንቅናቄው አንድነት ዋስትና ሊሰጠው ቻሏል::
የድርጅቱ መምሪያ ኮሚቴ ሥራውን ያለአንቀፋት ለማካሄድ እን
ዲያስቻለው ዋና ጽሕፈትቤቱ በኮናክሪ ከተማ ላይ በመሆኑ ባመ
ራሩ ምንም ዓይነት ቸግር ወይም አለመግባባት አልፈጠረም::
መሪዎቹ ብዙውን ጊዜ አገሩ ውስጥ ነጻ በወጡት ቦታዎቸ ሁሉ

አሳፊነታቸውን ተቀብለው ሲሰሩ ይገኛሉ::ያለበለዚያም በየጊዜው እየሄዱ ሁኔታውን በሰፍራው ላይ በመገኘት ይከታተሳሉ::

ምንም እንኳ ይህ ግንባር ንቅናቄውን 'ሶሺያሊስት' ወይም 'ማርክሲስት' የሚል ቅጽል ባይሰጠውም ትግሉ ከቀረው ዓለምአቀፍ ፀረኢምፔሪያሊስት ትግል በምንም እንደማይነጠል በተግባሩ ያሳያል::ለዚህም በአንዳንድ ቋሚ መሠረታዊ አሳቦች መመራቱ ተጨማሪ ምስክር ነው::ለምሳሌ ጥፋት ሲኖር ማጋለጥ: የአመራር ስህተት ሲሰራ ጥፋቱን አምኖ መፍትሄውን መፈለግ: የፖሊቲካውም ሆነ የጦሩ አመራር ከላይ እስከታች በየደረጃው ማህበራዊ መልክ እንዲኖረው ማድረግ:በተለይም ደግሞ ሬቮሉሽናዊ ዴሞክራሲ እንዲጠበቅ መጣር::

በዚህ ዓይነት ከብራል 'ሥልጣኑን ሊጨብጥ ይችላል' ስለሚባለው ብሄራዊ ቡርዡዋ መደብ ሲናገር 'ከሱ ዛሬ የሚፈለገው ራሱን እንዲያጠፋ ብቻ ነው'ይላል:: 'ምክንያቱም ሬቮሉሽኑ ከሥልጣን አርቆ የሠራተኛውና የገበሬው ታዛዥ ያደርገዋል::'ስለዚህም ከዚህ በተለይ ከካፕ ቬርዴ ዝቅተኛ ቡርዧዋመደብ የተውጣጣው ግንባር ቀደም ቡድን ከገበሬው ከተመለመሉትና በትግል ከዳበሩት ታጋዮች ጋር በመዋሃድ የዱሮ መደባዊ መልኩን ጨርሶ ማጥፋት አለበት::'

ጊኒ ቢሳው በአስራ ሶስት አውራጃዎች ሲከፋፈል እያንዳንዱ አውራጃ በወረዳዎችና በምክትል ወረዳዎች ይከፋፈላል:: አንድ ምክትል ወረዳ ብዙ መንደሮችን ሲጠቀልል:በየመንደሩ አምስት ሰው የሚገኝበት ሬቮሉሽናዊ ኮሚቴ ተቋቁሞበታል:: ከአምስቱ የኮሚቴ አባሎች ሶስቱ የግድ ሴቶች መሆን ሲኖርባ



ቸው /ይህ ራሱ አንድ ትልቅ መሠረታዊ ለውጥ ነው/ እነዚህም በፓርቲው ተመርጠው የመንደሩ ህዝብ እንዲቀበላቸው ያስፈልጋል::ኮሚቴው የመንደሩን ህዝብ በማደራጀት ለጠመንጃ ትግል የሚጠየቀበትን ትግል እንዲፈጽምና መምሪያዎችም በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል::የመንደሩ ህዝብ ህዝባዊው ጦር ጠላት ላይ አደጋ በሚጥልበት ጊዜ ጥይትና መሣርያ ከተከማቸበት ቦታ አምጥቶ ማቀረብ አለበት::ለአርበኞቹ የሚያስፈልገውን እህልና ወሀ ማቀረብ አለበት::በትግሉ በቀጥታ የሚሣተፉትን ሁሉ በሚገባ ለመመገብ ነጻ የወጡትን መሬቶች ማረስ አለበት::ይህ ጠቀላላ ተግባር የሚፈጸመው ያላንዳች ተሸከርካሪ መኪና ነው::ማንኛውንም ነገር በትከሻቸው ወይም በጭንቅላታቸው ተሸክመው ሲዘዋወሩ ከላይ የፖርቱጋል የጦር አኤሮፕላኖች የቦምብ ናዳ ያወርዱባቸዋል::ከሰባት ዓመታት ጀምሮ ህዝቡ ጫካውን ከለላ እንዲያደርግ ተገደአል::ያለዚያም ጎህ ሲቀድ ሠፈሩን ለቆ በየደኑ ተሰውሮ ይቆይና ጀንበር ስትጠልቅ ተመልሶ ይመጣል::በህዝቡ ውስጥ ህግ እንዲከበርና ጸጥታ እንዲጠበቅ ኮሚቴውን የሚያግዝ ከመንደሩ ሰው የተውጣጣ ህግ አስከባሪ ቡድን አለ::ይህ ህዝባዊ የጦር ኃይል በመንደሩ ላይ ጠላት አደጋ በሚጥልበት ጊዜ ቋሚው ጦር እስኪደርስ ድረስ መቋቋም ተጨማሪ ግዳጅ ነው::

## የገጠር ህክምና መስጫ ድርጅት

ዳኞቹ በህዝቡ የተመረጡባቸው የሠፈር ፍርድ ቤቶች ዝቅተኛ ወንጀሎችን ይፈርዳሉ::ከፍተኛ ወንጀሎችን የሚመለከተው የጦር ኮሚቴው ነው::ፍርድ ቤቶቹ የሚጠቀሙበት ካገሩ ወይም ከመንደሩ ነዋሪዎች ልምድ የመነጨ ሲሆን የፓርቲው የህግ ክፍል የሚያቀርበውን ማሻሻያ በማጠቃለል ነው::በትምህርትና በጤና በኩል ከባደ ተነሥቶ መሠረት መጣል ያስፈልግ ነበር::ከቸግሮቹ ዋናው የመምህራን አለመኖር ነበር::የትምህርት መስጫ

ክፍሎች በጣም ሰፋፊና ብዙ ልጆችን የያዙ በመሆናቸው የትም
ሀርቶን ደረጃ ዝቅ ለማድረግና ለጠላት የጦር አኤሮፕላኖች
ምቹ ዒላማ ለመሆን ቸለዋል::ይሁን እንጂ ዛሬ ነጻ አወጣው
አገር ውስጥ እስከ 15000 የተማሩ ወጣቶች ይቀጠራሉ::
ጎበዝጎበዞቹ ትምህርታቸውን በአዳሪነት በየጠቅላይ ግዛት ትም
ህርት ቤቶች ውስጥ እንዲቀጥሉ ይደረጋል:ከዚያም ከናከሪ ከተማ
ላይ ጀር ቶው ከቋሚው ከፍተኛ ትምህርት መስጫ ውስጥ ይላ
ካሉ:: የጤና የርሻ የመሀንዲስ ወዘተ:መኩንኖች የሚሰለጥኑት
የሶሻሊስት አገሮች ለእርዳታ በሚሰጡት የትምህርት እድል ነው::
300 ተማሪዎች በነዚህ አገሮች ዩኒቨርሲቲና ሁለተኛ ደረጃ
ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይገኛሉ::

ነጻ አወጣው አገር ውስጥ ሶስት ሆስፒታሎች የህክምና
እርዳታ ያለማቋረጥ ይሰጣሉ:: የጠላት አየር ሀይል በሚያደርገው
ጭፍጨፋ ምክንያት ቋሚ ድርጅቶች አቋቁሞ ለበሽተኞች የተሟላ
ህክምና ለመስጠት አልተቻለም::ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ
ሆስፒታሉ አቋሙን ጠቅሉ ከተቋቋመበት ቦታ ተነስቶ ሰፍራ መለ
ወጥ አለበት::ከባድ መቁሰል የደረሰባቸው ሁሉ በሰው ተከሻ
ላይ ተጭነው ወደጊኔ ሪፐብሊክ ቦኬ ከተማ ውስጥ ጀር ቲ ወዳ
ቋቋመው ሆስፒታል መሄድ አለባቸው::ወደሰሜን እንዳይሄዱ
ሲኔጋል ውስጥ ዚጊንቾር ከተማ ላይ የነበረው ሆስፒታል ስራ
ውን እንዲያቆም የሲኔጋል መንግሥት በቅርቡ አስገድዶታል::

የነጻነቱ ግንባር እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉትን
የፖሊቲካ የኤኮኖሚና የህብረተሰብ ድርጅቶች ለማቋቋም የቶን
ያህል እንደሚቸገር በትክክል ለመገመት ያዳግታል::የአገሩ
ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባህልና ወደኋላ የቀረ ልምዱ ማንኛ
ውንም ለውጥና መሻሻል ከመቀበሉ በፊት ሰፊ ማብራሪያና ረጅም



መረጃን ይጠይቃል:: ጀር ቲው ለምዱና እምነትን ፊትለፊት ለመ
ቃወምና ለመተና ነቅ አይፈልግም::አላማውንና ጥረቱን በበለጠ
ሊያራምድ የሚችለው ሃሳቡን ተቀብለው በሥራ ላይ ያዋሉት ሁሉ
ያስገኙላቸውን ጠቀሜታና መሻሻል ለሌሎች ለማሳየትና በማመሳከር
መሆኑን ተገንዝቦአል::ለምሳሌ ያህል ትግሉ ሲጀመር ባላገሩ
ለመዝመት መተት ያዘለ ጨሌና ደቃ ተሰጥቶት ካላንጠለጠለ አሻ
ፈረኝ ይል ነበር::

ይቀጥላል

Editorial Board
Ethiopian Students Union in Europe
P. O. Box 3198
Stockholm, Sweden

Dear brothers,

I received your very interesting publication, Tiglachin, through a friend. That is how I came to trace your address. I never dreamt that such a strong student organisation could exist, although far away from home.

Not only does Haile Sellasie's regime mercilessly massacre students and exploit the masses, as you have pointed out, but it is also waging a genocidal war against the peoples of Bale and Arussi. I am surprised to note that you have made no mention of these peoples' struggle for survival. Could it be that you are influenced by the regime's propaganda which claims that the fighters are "shiftas from Somalia"?

The situation in southern Ethiopia is quite tense. The green hills and highlands of Arussi are being turned into a barren desert. Its cattle wealth and crops are being reduced to ashes by the regime's bombs. Thousands of people are made homeless. Nevertheless, however strong the repression may be, the resistance movement of the masses is determined to carry out the struggle until final victory.

I would like to draw your attention to the fact that Haile Sellassie's regime has undertaken this genocide with the connivance of the imperialist world.



Advised and commanded by imperialist agents, the regime's armed forces have embarked on a systematic extermination of the unarmed people of Ginir, Hirane, Gidole, Doyna, etc. In these regions, water wells have been poisoned in the lowlands and forests set on fire on the highlands. Whole villages in Arussi have been wiped out through the same methods used by the Italian fascists against the Ethiopian peoples a quarter of a century ago.....

To the great dismay of the regime, the peoples' resistance movement is gaining momentum. In fact, it is spreading into Harar and Sidamo.

I have heard from a reliable source that fighting has recently broken out in Wallo and Tigrai against the infamous gabbar system. Today the Ethiopian masses have risen against Haile Sellassie's oppressive regime of illiteracy, hunger, disease, social inequality, injustice and exploitation.

Dear Brothers,

Let us, therefore, work for the common good of the masses, irrespective of religious, language and ethnical differences, while at the same time recognising the right of the people to carry out their just struggle for emancipation.

With fraternal greetings,
Robile Goden
Baghdad, Iraq

| ይዘት | ገጽ |
| --- | --- |
| 1. ያገር ቤት ዜና | 1 |
| 2. ለዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር | 5 |
| 3. ጊዜያዊ ችግሮችና የጊዜው ጥያቄ | 13 |
| 4. መልስ | 16 |
| 5. ከህዝቡ ጋር መዋሀድ የምንለው ይህ ነው | 28 |